የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፴፮
አዲስ አበባ — ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

3rd Year No. 36
ADDIS ABABA - 13th May, 1997

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፸፫/፲፱፻፹፱ ዓ.ም.
የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ........................................ ገጽ ፭፻፲፮

CONTENTS

Proclamation No. 73/1997
Ethiopian Radio and Television Agency Establishment (Amendment) Proclamation ............ Page 516

## አዋጅ ቁጥር ፸፫/፲፱፻፹፱
## የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅን ማሻሻል በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፸፫/፲፱፻፹፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· ማሻሻያ

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር ፩፻፲፬/፲፱፻፹፯ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፣

፩· የአንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) ተሠርዘው በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፫) ተተክተዋል፣
"፫/ አስፈላጊ የሆኑ ም/ዋና ሥራ አስኪያጆች"

፪/ የአንቀጽ ፮ ንዑስ አንቀጽ (፭) ንዑስ አንቀጽ (፬) ሆኗል።

፫· ከአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፮) ቀጥሎ የሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ (፯) ተጨምሯል።
"፯/ የድርጅቱን ጋዜጠኞች፣ የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ሠራተኞች የደመወዝ ስኬል፣ የቅጥርና የአስተዳደር መመሪያ ያወጣል።"

፬· የአንቀጽ ፰ ንዑስ አንቀጽ (፯)፣ (፰) እና (፱) እንደቅደም ተከተላቸው ንዑስ አንቀጽ (፰)፣ (፱) እና (፲) ሆነዋል።

## PROCLAMATION NO. 73/1997
## A PROCLAMATION TO AMEND THE ETHIOPIAN RADIO AND TELEVISION AGENCY ESTABLISHMENT PROCLAMATION

WHEREAS, it has become necessary to amend the Ethiopian Radio and Television Agency Establishment Proclamation;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Radio and Televsion Agency Establishment (Amendment) Proclamation No. 73/1997."

2. *Amendment*

   The Ethiopian Radio and Television Agency Establishment Proclamation No. 114/1995 is amended as follows:

   1/ Sub-Articles (3) and (4) of Article 6 are hereby deleted and replaced by tthe following new-sub-Article (3):
   "3) the necessary deputy General Managers:"

   2/ Sub-Article (5) of Article 6 is renumbered as sub-Article (4).

   3/ The following new sub-Article (7) is added after sub-Article (6) of Article 8;
   "7) issue directives on the salary scale, employment and administration of journalists as well as the production and technical staff of the agency."

   4/ Sub-Articles (7), (8) and (9) of Article 8 are renumbered as sub-Articles (8), (9) and (10), respectively.

፭· የአንቀጽ ፲ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ ፫(ለ) ተተክቷል ፡

"ለ/ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ጋዜጠኞችን፣ የፕሮዳክሽንና የቴክኒክ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣ ደመወዝና አበላቸውንም ይወስናል። የድርጅቱን ሌሎች ሠራተኞች በፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረት ይቀጥራል ፡ ያስተዳድራል።"

፫· <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፭ ቀን ፲፱፻፹፱ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ

ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

5/ Sub-Article (3) (b) of Article 10 is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article (3) (b):

"b) employ and administer as well as fix the salaries and allowances of journalists and the production and technical staff in accordance with the directives issued by the Board; employ and administer the other staff of the Agency in accordance with federal civil service laws."

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 13th day *of May, 1997.*

Done At Addis Ababa, this 13th day of May, 1997.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC

REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት
BERHANENA SELAM PRINTING PRESS